# ዝርዝርና ጥቅልል

ወንዶችንና ሴቶችን በተመለከተ ከተጻፉ መጻሕፍት መካከል ከርእሱ ጀምሮ የሚገርመኝ አንድ መጽሐፈ አለ፡፡ «why Men Don't have a clue & Women always need more shoes» ይላል፡፡ ባልና ሚስቱ የመጽሐፉ ደራስያን አላንና ባርባራ ፔዝ የወንዶችንና የሴቶችን ግንኙነት ጤናማና ሰላማዊ ለማድረግ አንዱ ዋናው መንገድ ሁለቱ በነገሮች ላይ ያላቸውን ልዩነት ጠንቅቆ ማወቅና በዚያ ላይ ግንኙነትን መመሥረት ነው ይላሉ፡፡

በመጽሐፉ ውስጥ ካነሷቸው አስገራሚ የወንዶችና ሴቶች የአነዋወርና አስተሳሰብ ልዩነቶች መካከል አንዱ ነገሮችን የሚያዩበት መንገድ ነው፡፡ ሴቶች ነገሮችን በዝርዝርና አበጥረው የማየት አዝማሚያና ተሰጥዖ አላቸው ይላሉ፡፡ ለምን? እንዴት? የት? ከዚያስ? እያሉ ነገሮችን ይፈተፍቷቸዋል፡፡ ወንዶቹ ‹ዝርዝር ኪስ ይቀዳል› በሚለው የአራዶች መመሪያ ተመርተው ነው መሰል ነገርን በጥልቁና በዝርዝሩ ከማየት ይልቅ ጠቅላላውን ነገር ስለሚመርጡ ስለ አንድ ጉዳይ በዝርዝር ሲጠየቁ ቁጥጥር የተደረገባቸው፣ ምርመራ የተካሄደባቸውና አለመታመን የተፈጠረባቸው መስሏቸው ቁጣ ይቀድማቸዋል፡፡ ነገሩ የመጣው ጉዳዮችን በዝርዝር በሚያየው የሴቶች ልቡናና ነገሮችን መጠቅለል በሚወደው የወንዶች ልቡና መካከል በተፈጠረ ልዩነት ነው፡፡

እዚህ ላይ እንዲያውም አንድ ምሳሌ ያነሳሉ፡፡ በአንድ ግብዣ ላይ ወንዶችና ሴቶች በየጠረጴዛቸው ከብበው ሲጫወቱ ብታዩ ሴቶቹ ጋ ብዙ ማኅበራዊ፣ ቤታዊ፣ ልጃዊና ትዳራዊ ጉዳዮች እየተነሡ ሲበለቱና ሲተነተኑ ትሰማላችሁ፡፡ የማይተዋወቁት ሴቶች ከመተዋወቅ አልፈው የቤታቸውን ጓዳ ገላልጠው ሲወያዩበትና ሲማማሩበት ትመለከታላችሁ፡፡ ሴቶቹ ከስም አልፈው መቼ እንዳገቡ፣ ስንት ልጆች እንዳሏቸው፣ የት እንደሚኖሩና ምን እንደሚሠሩ፣ ሌላው ቀርቶ የቤት ሠራተኞቻቸውን ጉዳይ ሳይቀር ተነጋግረዋል፡፡ ወዲያኛው ጠረጴዛ ያሉትን ከአንድ ሰዓት ጨዋታቸው በኋላ ብታዩዋቸው ግን እንደዚያ እየተሳሳቁና ድምጻቸውን ሞቅ አድርገው እየተጫወቱ የነበሩት ወንዶች፣ እንኳን የልጆቻቸውን ቁጥር የራሳቸውን ስም እንኳን እርስ በርስ ላይተዋወቁ ይችላሉ፡፡ ማነው? የት ነው የሚኖረው? ትዳር አለው ወይ? ትዳሩስ እንዴት ነው? የሚለው ፈጽሞ ላይነሣ ይችላል፡፡ ምናልባትም ስለ ስፖርት፣ ፖለቲካ ወይም ደግሞ ስለ ሰሞኑ የከተማው ወሬ እየተወራ ይሆናል፡፡

ሴቶቹና ወንዶቹ ከግብዣው በኋላ ወደየቤታቸው ሲሄዱ ‹እንትናኮ እንዲህ አለችኝ» ትለዋለች ሚስቱ፡፡ «የቷ ናት እንትና» ይላል እርሱም፡፡ «የእንትና ባለቤት» ትልና አብሮት ሲጫወት የነበረውን ሰው ስም ትነግረዋለች፡፡ ሴቶቹ ስለ ራሳቸው ብቻ ሳይሆን የባሎቻቸውንም ማንነት ተዋውቀዋላ፡፡ «የቱ ነው እንትና» ይላል፡፡እርሱ እቴ አብሮ ተጫወተ እንጂ ስሙን አያውቀው፡፡ «የትኛው ነበረ ባክሽ» ከዚህ በኋላ ማስታወሱ መከራ ነው፣ ይላሉ አላንና ባርባራ ፔዝ፡፡

‹አንዴ› ይላሉ ደራሲዎቹ ‹ዩልያንና ሐና የሚባሉ ባልና ሚስት ነበሩ፡፡ የባልየው የድሮ ጓደኛ ራልፍ ከዓመታት በኋላ መጣና ጎልፍ ሜዳ ሲገናኙ ከዩልያን ጋር ተቃጠሩ፡፡ ቀኑን ሙሉ ሲጫወቱ ውለው ዩልያን ወደ ቤቱ ሲመለስ የጠፋው የባሏ ጓደኛ ከብዙ ጊዜ በኋላ በመምጣቱ የገረማት ሚስት «ቀኑ እንዴት ነበር» አለቺው ባሏን፡፡

«አሪፍ ነበር» አለ ዩልያንም፡፡

«ራልፍስ ደኅና ነው›»

«ደኅና ነው»

«ባለቤቱ ከሆስፒታል ከወጣች በኋላ እንዴት ናት» አለቺው

«አልጠየቅኩትም- እርሱም ምን ነገር አልነገረኝም» አለ ዩልያን፡፡

«አልነገረኝም? አንተም አልጠየቅከውም?»

«አልጠየቅኩትም፡፡ ግን አንዳች ነገር ብትሆን ኖሮ ይነግረኝ ነበር»

«ልጃቸውስ፣ ከአዲሱ ባሏ ጋር ተስማማች»

«ምንም ነገር አላለኝም፡፡

«የራልፍ እናት አሁንም ኬሞቴራፒውን እየወሰዱ ነው፤ ለመሆኑ የተለየ ነገር አለ?»

«እኔ እንጃ»

«ታድያ ቀኑን ሙሉ ምን ስታወሩ ነው የዋላችሁት?»

«ጎልፍ ተጫወትን፣ ስንቀልድ ነበር፤ ሌሎች ጓደኞቻችንን መጡ፣ በቃ ስንጫወት ዋልን»

ይኼ ጉዳይ በሁለቱ ጓደኛሞች መካከል ብቻ አይደለም የሚፈጠረው፡፡ በባልና ሚስቱም መካከል ጭምር እንጂ፡፡ ሚስቶቹ ነገሮችን በዝርዝርና አንድ በአንድ መነጋገር፣ ማወቅና መረዳት ይፈልጋሉ፡፡ ባሎቹ ደግሞ ስለ ጉዳዩ ከሰሙ በቂያቸው ነው፡፡ አንድ ሰው እንዲያውም ‹ወንዶች ሚች ማን እንደሆነ ሳያውቁ ልቅሶ መድረስ ይችላሉ» ብሏል፡፡ እዚያ ልቅሶ ቤትም ሄደውም ካርታ መጫወት፣ የሰሙኑን ፖለቲካና የስፖርት ወሬዎችን መሰለቅ ካልሆነ በቀር ለቀስተኞችን ቀርበው ላይጠይቋቸው፣ ምን ሆኖ ሞተ? ሕክምና ወስዶ ነበር ወይ? ከዚህ በፊት ታምሞ ነበር ወይ? ላይሉም ይችላሉ፡፡

ወንዶቹ ነገሮችን ጠቅልሎ የማየት አዝማሚያ አላቸው፡፡ ለወንዶች ወጡ ወጥ ነው፡፡ አንድ ድስት ወጥ፡፡ ለሴቶቹ ግን ወጡ ብዙ ነገር ነው፡፡ ሽንኩርት፣ ቅመም፣ ዘይት፣ እህል፣ እሳት፣ ድስት፣ ማማሰያ፣ ሞያ ነው፡፡ ወንዶቹ «ወጡ አይጣፍጥም» ነው የሚሉት፡፡ ሴቶቹ ግን ‹ጨው አንሶታል፣ ሽንኩርቱ በደንብ አልተቁላላም፣ ቅመም በዝቷል፣ በርበሬው አርሯል» ብለው ይተነትኑታል፡፡ ለወንዶች ዋናው ድምር ውጤቱ ነው፤ ለሴቶች ግን ዋናው ድምሩን ያመጡት ቅንጣቶች ናቸው፡፡

አለንና ባርባራ ይኸ ጉዳይ ለምን መጣ? ለሚለው ጥያቄ የሚያቀርቡት አንዱ ምክንያት የሰው ልጅ አነዋወሩን ቀየረ እንጂ የማሰቢያ ንጥረ ነገሩን አልቀየረም የሚለውን ነው፡፡ ሰው በምድር ላይ ኑሮ ሲጀምር የመጀመሪያ ሥራው አደን ነበር፡፡ ወንዶቹ ሊያድኑ ይወጣሉ፡፡ ሴቶቹ ልጆቻቸውን ይዘው ቤት ይሆናሉ፡፡ የሰው ልጅ የማሰቢያ መንገድ የተቀረጸው ያኔ ነው፡፡ አሁንም በአደን መንገድ ነው እያሰበ የሚኖረው ይላሉ፡፡ ለምሳሌ ወንዶች አንድ ቦታ ሰብሰብ ብለው፣ ነገር ግን ሁሉም ዝም ብለው በየራሳቸው ዓለም ሲጓዙ ታዩ ይሆናል፡፡ በዚያው ወቅት ግን ሴቶቹ አንድ አካባቢ የቀለጠ ወሬ ይዘዋል፡፡ ነገሩ የተፈጠረው ወንዶች ዝምተኛ ሴቶች ደግሞ ወሬኞች ስለሆኑ አይደለም፡፡

በአደን ዘመን ወንዶቹ ለአደን ይወጣሉ፡፡ ግዳይ እስኪያገኙ ድረስ ወጥመዳቸውን አጥምደው አለያም ደግሞ መሣሪያቸውን አነጣጥረው ይጠብቃሉ፤ ይሸምቃሉ፣ያደባሉ፡፡ አደን አንድ ከፍተኛ ከሂሎት ይጠይቃል፤ በግዳዩ ላይ በጥንቃቄ ማነጣጠር፡፡ ስለዚህም ወንዶቹ አንድ ቦታ ቢከብቡም እንኳን ሁሉም ግን በዝምታ ግዳያቸው ላይ ማነጣጠር ይፈልጋሉ፡፡ በተቃራኒው ሴቶቹ ባሎቻቸው ከወጡ ሰንብተዋል፡፡ በሰላም ይመለሱ ይሆን? የሚለው ሥጋት አለ፡፡ ሥጋቱን ማቃለል የሚችሉት እርስ በርስ በመነጋገርና በመጽናናት ነው፡፡ ከዚያም በላይ ቀኑን የሚሳልፉት በቤት ሥራ ነው፡፡ የሚመጣውን ችግር ለመወጣትም በአንድ አካባቢ ይሆናሉ፡፡ ይነጋገራሉ፣ ይወያያሉ፤ መፍትሔ ይወራረሳሉ፤ ለዝርዝሮች ጊዜ ያገኛሉ፡፡ ወንዶቹ ከግዳይ በኋላ ወደ ቤት ሲመለሱ እንኳን እሳት ከብበው ዝምታን ሊመርጡ ይችላሉ፡፡ የአራዊቱ ሁኔታ፣ ጫካው፣ የአደኑ ቅደም ተከተል፣ ከሞት ያመለጡበት አጋጣሚ፣ የቀጣዩ ጊዜ አደን በዝምታ ይታሰባል፡፡

ለወንዱ ጉዳዩ ‹አንበሳ ገዳይ› የሚለው ላይ ያልቃል፡፡ ዋናው አንበሳ መግደሉ ነው፡፡ ለሴቶቹ ደግሞ እንዴት? መቼ? ለምን? የሚለው ሁሉ አስፈላጊ ነው፡፡ ከዚህ ይልቅ ያ፣ ከእንዲህ ይበልጥ እንዲያ ለምን አልሆነም? የሚለውም ወሳኝ ነው፡፡ ይህንን ግን ወንዶቹ እንደ ጭቅጭቅና ንዝንዝ ያዩታል፡፡

አንድ ሌላ ባለሞያ ይህንን ነገር ‹በወንዶች አእምሮ ውስጥ በየራሳቸው የተቀመጡ ልዩ ልዩ ሳጥኖች አሉ፡፡ የሴቶች አእምሮ ግን እርስ በርሳቸው በተገናኙ ሽቦዎች የተሞላ ነው፡፡ ለወንዶች አንድ ጉዳይ ማለት አንድ ሳጥን ነው፡፡ ከሌላው ሳጥን ጋርም ምንም ግንኙነት የለውም፡፡ አንዱ ሳጥን ሲከፈትም ሌሎች ይዘጋሉ፡፡ ነገሮችን ሳጥን በሳጥን ማየት ይመርጣሉ፡፡ አያገናኟቸውም፡፡ ለሴቶች ግን ነገሮች እርስ በርሳቸው የተገናኙ ናቸው፡፡ በየራሳቸው እየተነተኑና እያያያዙ ማየትንም ይመርጣሉ፡፡ ከወንዶች ሳጥን ውስጥ የሚገርመው ‹ባዶ ሳጥን› የሚባለው ነው፡፡ አንድን ወንድ ዝም ብሎ ቁጭ ብሎ ብታገኙትና «ምን እያሰብክ ነው?» ብትሉት «ምንም» ሊላችሁ ይችላል፡፡ እየደበቃችሁ አይደለም፡፡ ምንም ሳያስብ ለረዥም ጊዜ ዝም ማለት የሚችለው ‹ባዶ ሳጥኑ› ሲከፈት ነው፡፡ እዚያ ውስጥ ምንም የለም፡፡ የሴቶች አእምሮ ግን የተጠላለፈ ሽቦ በመሆኑ አንድን ነገር የሚያስቡት ከሌላ ነገር ጋር አያይዘው ነው፡፡ ወንዶች ሴቶች የተጠራጠሩ ወይም የሚመራመሩ የሚመስሏቸው ነገሮችን አያይዘው ስለሚያዩ ነው፡፡

«ይኼንን ነገር ነው ዛሬም የምናየው» ይላሉ ባለሞያዎቹ፡፡ ‹አንበሳ ገዳይ› በሚለው አስተሳሰብ ለተቃኘው ወንድ የሚገዛ ነገር ዝርዝር ይዞ፣ ገበያ ወርዶ፣ አማርጦና ተከራክሮ መግዛት ከባድ ነው፡፡ የልብስና ጫማ ገበያ ገብቶ ሳይሰለች እየተዘዋወረ ቃኝቶ መግዛት ምጥ ነው፡፡ ዋጋ ለማወዳደር፣ በየገበያው ገብቶ ማነጻጸር ሸክም ነው፡፡ ከዚያ ይልቅ በመሰለው ዋጋ አንዱን ገዝቶ ሳይከራከርና ሳያማትር መውጣትን ይመርጣል፡፡ አንድ መረጃ እንደጠቆመውም ቤታቸውን በሚያሠሩ ባለትዳሮች ዘንድ ሚስቶች የሚያሠሯቸው ቤቶች ባሎች ከሚያሠሯቸው ቤቶች ይልቅ ዋጋቸው ቢያንስ 40% ይቀንሳል፡፡ አንድ ወዳጄ እንዲያውም ‹አንበሳ መግደል› የሚለው ብሂል ይሆን እንዴ አትክልት ተራና ዕቃ ተራ ሄደው ከመግዛት ይልቅ በሬ ተራና በግ ተራ ወርደው መግዛት የወንዶች ሆኖ የቀረው? ብሎኛል፡፡

በወንዶችና ሴቶች ግንኙነት ውስጥ ጤናማ ከባቢን ለመፍጠር አንዱ መንገድ ልዩነቶቻችን ዐውቀን፣ በልዩነቶቻችን ውስጥ እንዴት እንደምንኖር፣ ከልዩነቶቻችንም እንዴት እንደምናተርፍ አስበን መኖር ነው፡፡ ለምን እንዲህ አይሆንም ? ብሎ ከመጨቃጨቅ ይልቅ እንዴት እንዲህ ሊሆን ቻለ? እንዴትስ እንዲያ እንዳይሆን ማድረግ ይሻላል? የሚለውን መረዳቱ ይበልጥ ይጠቅመናል፡፡ ባልና ሚስት ሆነን የምንኖርበት ምክንያቱ ጉድለቶችን ለመሟላት ነውና በጎደለው ላይ ከመናደድ ይልቅ የጎደለውን መሙላቱ ቤቱን ‹ሙሉ› ያደርገዋል፡፡